# ፍርድን ለራስ ምርትን ለአግማስ (ቁጥር 3)

........................................ካለፈው የቀጠለ

የኢህአፓ መዋቅራዊ መስተዳደር በቀጠናዎች የተከፋፈለ ነው:: የፋሲካ ሰሜን አሜሪካ ሲሆን የመርሻና የኢያሱ ደግሞ አውሮፓ ነው። የሁሉም ቀጠናዎች ማዕከል ግን ዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ የሚገኘው እስፒክ በመባል የሚታወቀው መ/ቤት ነው። ያንጃው መሪ ካይሮ ላይ እንደወጣ ከመቅረቱ በፊት ይህ መሥሪያ ቤት በቁጥጥሩ ሥር ነበር። በሁዋላ ግን ይህ መሥሪያ ቤት መስተዳደሩ በፋሲካ በለጠ ስር ሲሆን የመርሻ ዐይን መቅላት ጀመረ። ይህንንም ለውጥ ተከትሎ ቅናት የሚሉት በሽታ ወገቡን አጥመነመነው። ዳሩ ለወገቤ መታሻ ይበጀኛል ያለው መዳህኒት ግን አሉባልታ ነበር። “ፋሲካ አምባ ገነን እየሆነ ነው” የሚል። ይልቁንም ፋሲካን አየሁ አውሬ አየሁ እየሆነበት ግንኙነቱን ይበልጥ አሻከረው። ከዚህ በሁዋላም ኢህአፓ እንደ አንድ ሰው ማሰብና እንደ አንድ ሰው መናገር እየተሳነው መጣ። ይልቁንም ባኢን ጎዳሁ ብላ እንገቷን በጋሬጣ እንዲሉ በነ በየነ ጉራ በኩል ለሳልሳዊ ወያኔዎች ለነ አረጋዊ በርሄ፣ በነ ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው በኩልም ለወያኔው ሰላይ ለኤልያስ ክፍሌ የድርጅቱን ምስጢር መዘክዘክ ጀመረ። ውሎ አድሮም መርሻ ጀጀባውን ሲሉት አረፋውን እየጨበጠ ወደ ጥፋት ባህር መዝቀጡን ሙያየ ብሎ ቀጠለበት።

የአንጃው መሪ ነገረ ሥራው ሁሉ ወያኔ ወያኔን እየቀነሰ በመጣ ቁጥር ባመራር አካላትና ባባላትም ዘንድ ተዓማኒነቱን እያጣ ሄደ። ዛሬ ገልብጦ ወያኔ ተባልኩ በማለት ለማጣወር የሚፈልገው ይህኑ ሀቅ ነው። ዕምነቱ እየሚሸሸ በሄደ ቁጥር አንጃዊ ሥራውም የዚያኑ ያክል እየጠነዛ መጣ ; ቅርበቱ ከወደ ጓዶቹ መሆኑ ቀርቶ ከወደ ኢህአፓ ጠላቶች እየተጠጋ መጣ። ከነ ዶ/ር ፍስሃ አበበ፣ ከሰደዱ ካድሬ ከነ ዓለሙ ያይኔ፣ ከነ አንዳርጋቸው ፅጌ፣ ከነ ክፍሉ ታደሰ፣ ከነ ኤልያስ ክፍሌ፣ ከነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋና መሰል ቅጥረኞች ጋር አርከይ አርከይ መባባል ጀመረ። እነርሱንም ለማስደሰት “ኢህአፓ በድርጅቶች መሃል ጣልቃ እየገባ፣ ሁሉን እኔ ካልመራሁት በሚል ትምክህት ድርጅቶችን እያፈረሰ“ ወዘተ ብሎ ሰላሳ አምስት ዓመት የታገለበትንና ከሃያ ዓመት በላይም የመራውን ድርጅት በውሸት ከሰሰ። ጅራፍ ራሷን ገረፋ ራሷው ትጮህ እንዲሉም ራሱን በራሱ በውሸት ወነጀለ።

የመለያየታችንም ዋነኛው ምክኒያት ኢህአፓ በድርጅቶች መሃል ጣልቃ መግባቱ ነው በማለት የነ ዶ/ር ብርሃኑን ልብ ሊበላ ሞከረ። ይህ ሁሉ ልፋት ግን በዶ/ር ብርሃኑ በኩል ተረማምዶ ከወያኔ ጋር ለመሞዳሞድ መሆኑ ከማንም ህሊና የሚሰወር አይደለም። ይልቁንም የተያዘው ጥድፊያ፦

- **ቶሎቶሎ እንበል ጊዜ ሮጦ አምልጧል**
- ሳንይዘው አልፎን ቀድሞን ተለውጧል
- እንዲሉ በአለቀ ዕድሜ ለስልጣን እሩጫ ነው።

ኢህአፓ የህዝብ ንብረት፣የህዝብ አለኝታና፣የልዕዋላዊነት ሰንደቅ፣ ነው። ኢህአፓ የአንድነት ፈርጥ፣የጀግንነት አርማና የኢትየጵያዊነት ምኩራብ የደም ሃውልት ነው። ዳሩ ሃውልቱ ፈረሰ የሚሉ ካሉ ተሳስተዋል። የኢህአፓ መቀመጫ የህዝብ ልብ ነው። ሃውልትነቱም ኢትዮጵያዊነት ነውና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እስካሉ ድረስ ኢህአፓ ዘላለማዊ ሃውልት ሆኖ ይኖራል። ዛሬም ነገም እስከ ወዲያኛው ድረስ። ኢትዮጵያና ኢህአፓም በጀግኖቹ ልጆቻቸው መስዋዕትነት ተከብረው ይኖራሉ። አራት ነጥብ!

ሰው ማለት እንዳኖሩት የሚገኝ ሰው ነው ይሉ ነበር አያቴ። ነብሳቸውን ይማረውና። በርሳቸው ዘመን የነበረው ትውልድ ቃል ከሽክም ይከብዳል ብሎ የሚያምን ተውልድ ነበር። የኔ ትውልድም ከአያቶቹና ከቅድመ አያቶቹ የወረሰውን ዕምነት የአንገቱ ማተብ አድርጎ የትግሉ ነው ህይዎቴ ፍጹም ነው ዕምነቴ በማለት ንዑድ ህይዎቱን ለሀገሩና ለህዝቡ ቤዛ አድርጓል። ያ፡ ትውልድ ቃሉን የማያጥፍ፣ እንዳኖሩት የሚገኝ ተዓማኒነቱ ለህሊናው ለህዝቡና ለሀገሩ ዘነፍ የማይል ትውልድ ነበር። ግና ግና አንዳንድ ጊዜ ከስንዴው መሃል እንክርዳድ አብሮ እየበቀለ የሰብሉን ጥራት ሲያበላሸው ተስተውሏል። እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ05/30/08 አትላንታ ላይ የታዘብነው ነገር ቢኖር ይህንኑ እንክርዳድ ነበር።

ባለፈውና በወደፊቱ መካከል በተሰኘው መደብኪ

> *“since the lair free to fashion his facts to fit the profit and pleasure,or even the mere expectations, of his audience, the chances are that he will be more persuasive than the truth teller”*

እንዳለችው ሃና አረንዳት ያንጃው መሪ የውሸቶቹን ዓይነቶች እያቀያረ ዕውነታዎችን ለፖለቲካ ገበያ በሚያመቹ መንገዶች ለሸቀጥ አቅርቧቸዋል። አዳማጮቹ መስማት የሚፈልጉትን ነገር በመናገር የኢህአፓን ጠላቶች ድጋፍ

ለማግኘት ችሏል። ያነጀው መሪ ድርጅቱን በውሸት ሲወነጅል “ኢህአፓ ያባላቱን መብት አያከብርም። አባላቱንም በእኩልነት አያይም። በውስጡ ዲሞክራሲ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የለም..” ሌላም ሌላም ብሏል። ይህን ውሸት ያዳመጡት የሰደዱ ካድሬ ዓለሙ ያይኔና የወያኔው የዕባብ ልብስ ዶ/ር ፍስሀ አበበ “ኢህአፓ አይደለም አንድ ጊዜ ዘጠኝ ጊዜ መከፋፈል ሲያንሰው ነው”(ዓለሙ)፤ “የኢህአፓ መከፋፈል ዕመርታ ነው። ዕድገት ነው።” (ዶ/ር ፍስሃ) እነዚህ ሁለት ወንጀለኞች ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ገና ያላወራረዱት ሂሳብ አላቸው። አንደኛው በደም። ሌላኛው ደግሞ በክህደትና በጁ-አዳፋነት። እነዚህ ሁለት ፀረ-ህዝቦች ለሱፍ አበባዎቹ ለነ ተስፋሁን አረጋዊ የዛሬ ወዳጅ ቢሆኑ ማንንም አይደንቀውም። ለምን? ቢባል ድሮውንም ውሻ ቅርሻቱን መላስ ተፈጥሮው እንጂ ነውሩ ስለአይደለ የተስፋሁንና የዓለሙ ያይኔ ሰሞነተኛ ፍቅር የውሻ ባህሪይ ነው።

የሱፍ አበባው ተስፋሁን የነ አዳነ ቢራራን፣ የነ ዘዋለ ዘገየን፣ ነጋ በለውን፣ ፈንቱ ገላውን፣ፀጋየ ዘገየን፣ የነ ዮሀንስ አስረስን፣ እንደ ዳሮ ነጋሽ ከፀንሷ ጋር የተረሸነቸውን የዕማዋይሽ ፈንቴን፣ አስገዳይ የሰደዱን ካድሬ ጓዴ ቢለው ዛሬ ማንንም አያስገርምም። ከኢህአፓ ጠላቶች ጋር ወግኖ አንጃ በሰማዕታቱ ደም ቢሳለቅ የክህደት ባህሪው ነውና አይገርመንም። የሚገርመን ነገር ቢኖር ሰኔና ሰኞ ሲገጣጠሙ እንድንል በስልጣን ጥማት፣ በመድረክ እታይ እታይ ባይነት፣ በዝና ፍለጋና በውሸት ክህሎት መርሻና ተስፋሁን አንድም ሁለትም መሆናቸው ነው።

ገበያ ውጣ አምሳያህን አታጣም እንዲሉም ዓለሙና ፍስሀ የመርሻንና የተስፋሁንን ባህሪይ የተላበሱ የሱፍ አበባዎች ናቸው። ዓለሙ ያይኔ ገና ፖለቲካ “ሀ” ብሎ ሲጀምር መኤሶን ነበር። የባንዳው ቡድን ቀኝ መንገደኛ ተብሎ መታደን ሲጀምር ዓለሙ ወደ ሰደድ ተሸጋሸገ። ሰደድና ፋሽሽቱ ደርግ ሲወድቁም መጀመሪያ ኢዴፓ በሁዋላ ቅንጅት ቀጥሎም የዶ/ር ብርሀኑ አንጃ ጋሻጃግሬ ሆነ። በቅርቡ ደግሞ ከወያኔው ቀንስላ ፀሀፊ ከታዬ እስቀ ጋር የድንበር ኮሚሽን አባል ሆኗል።

ዶ/ር ፍስሀስ? ዶ/ሩ ቀደም ሲል የኢህአፓ አባል ነበር። ከዚያም ድርጅቱን ከድቶ ወደ ሱዳን ብሎም ወደ ኬንያ ፈረጠጠ። ይህም ሰው መጀመሪያ የመድህን የጎሹ ወልዴ አጃቢ ቀጥሎ የልደቱ በሁዋላም የቅንጅት ደጋፊ ነበር። ይህን ሁሉ ሲያደርግ ግን የወያኔ ማሊያውን ሳያወልቅ ነበር። በቅር ቡም የብርሃኑ ነጋ አንጃ ደጋፊ ሆኗል። ባንድ ወቅትም ባትላንታ የሚሊኒየም- ጎንደር ተወካይ ነበር። በቅርቡም ከወያኔው ካድሬ ከአሰግድ ጋር ሆኖ የውጭውን ሲኖዶስ ለማፍረስ ሲዶልት ተነቅቶበት ተጋልጧል። ፍስሀ ቀን ቀን ከተቃዋሚ አመሻሹ ላይ ግን አዳሩ ከወያኔ ጋር የሆነ ሌላው የሱፍ አበባ ነው። አሁን ደግሞ የድንበር ኮሚሽኑ ሊቀ መንበር ሆኖ ድንበራችንን ሰጥቶ ሊያስመልስልን ተሰልፏል።

እነዚህን መሰል ሰዎች ከጎኑ አሰልፎ ነው አንጃው ወደ ህዝብ ዘልቀን ገብተናል የሚለን። ህዝብ ግን ራሱንና አገሩን መከላከል ከፈለገ ከወያኔ መሬት አሻሻጮች ነፃ የሆነ አካል ፈጥሮ መታገል ይጠበቅበታል። ይህን ሲያደርግ ነው ፍርድን ለራስ ምርትን ላግማስ እንዲሉ ከህሊናው ጋር ሊታገል የሚኖርበት። ከፍርዶች ሁሉ የህሊና ፍርድ ቀዳማይና የበላይ ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው በጆሮው የሰማውንና በዐይኑ ያየውን እንደ ወረደ የምስክርነት ቃሉን በመስጠት የዕውነትን ህላዌነት ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። ይህም ሲሆን ብቻ ነው ፍርደ-ህሊና ዳኝነት መስጠት የሚችለው። ጨረስኩ።

አብራሃም በየነ